



# ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ከቤተሰቦች እና አነሰተኛ ቡድኖች ጋር ውይይት ማካሄጃ ሰዕላዊ መወያያ መርጃ

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE

Breakthrough ACTION FOR SOCIAL & BEHAVIOR CHANGE

# የአጠቃቀም መመሪያ

የዚህ ስዕላዊ መማሪያ ዓላማ ህብረተሰቡ ከእንስሳት ወደሰው ስለሚተላልፉ በሽታዎች መሰረታዊ ግንዛቤ ኖሮት የራሱንና የቤተሰቡን ጤና እንዲሁም አካባቢውን ከብክለት እንዲጠብቅ ለማስተማር እና ለማነሳሳት የተዘጋጀ ነው።

ስዕላዊ መግለጫው ከእንስሳት ወደሰው የሚተላልፉ ሶስት ዋና ዋና በሽታዎችን ማለትም በአባሰንጋ፣ በሚያሳብድ የውሻ በሽታ እና በውርጃ በሽታ ላይ ያተኩራል። አወያዮች እንዳስፈላጊነቱ በሶስቱም በሽታዎች ዙሪያ ወይም በአንዱ ላይ ትኩረት ሰጥተው ውይይት ሊያደርጉ ይችላሉ። ከእያንዳንዱ ምስል ጀርባ ለውይይቱ የሚጠቅሙ ጥያቄዎች እና የተለያዩ ቁልፍ መልዕክቶች ተቀምጠዋል።


ይህን ስዕላዊ መማሪያ ለመጠቀም በእያንዳንዱ ገጽ ላይ የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች መከተል አስፈላጊ ነው።

1. ሊያወያዩበት የፈለጉትን የበሽታ አይነት በቀላሉ ለመለየት እንዲያስችል ማውጫው በስተግርጌ ተቀምጧል።
2. ውይይቱ ከመጀመሩ በፊት ራሳችሁን አስተዋውቁ። ለውይይታችሁ የሚረዱ ጥያቄዎችን እንደምትጠይቁ ነገር ግን ለጥያቄዎቹ ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ መልስ ያላቸው ሳይሆኑ ውይይት ለማድረግ ታስበው የተዘጋጁ እንደሆኑ እና ተወያዮች ስሜታቸውን ሳይፈሩ እና ሳይሸሽጉ እንዲገልፁ አበረታቷቸው።
3. ውይይቱን ስታካሂዱ በምታወያዩበት ገፅ ላይ ያለውን ምስል ለተወያዮች አሳዩ፤ ከምስሎቹ ጀርባ ያሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ በመጠየቅ ሁሉም ተሳታፊዎች እድል እንዴያገኙ በማድረግ ውይይቱን አካሂዱ።
4. በእያንዳንዱ ምሰል ላይ ማጠቃለያ ለመስጠት ከስር የተዘረዘሩትን ቁልፍ መልዕክቶች ተሳታፊዎችን በደንብ አስይዙ።
5. በእያንዳንዱ ገፅ ላይ የተቀመጡት መልዕክቶች ተሳታፊዎች አንደገባቸው ሳታረጋግጡ ወደሚቀጥለው ገፅ አትሂዱ።




# የአባሰንጋ በሽታ

# የአባሰንጋ በሽታ



# የአባሰንጋ በሽታ



# የአባሰንጋ በሽታ ምንነት?

## የመወያያ ነጥቦች

- በቤታችሁ ምን ምን እንስሳት አሉ?
- እነዚህ እንስሳት በድንገት ታመው ወዲያው እንዲሞቱ ሊያደርግ የሚችል በሽታ ይኖራል? ምን ይመስላችኋል?
- ይህ በሽታ በአካባቢያችሁ በእንስሳት ላይ ጉዳት አስከትሎ ያውቃል? በሰዎችስ ላይ? ጉዳቱን እንዴት ትገልፁታላችሁ?



## ቁልፍ መልዕክቶች

- እንስሳትን በድንገት ከሚገድሉ በሽታዎች አንዱ የአባሰንጋ በሽታ ነው፡፡
- በሽታው በዋናነት ሣር የሚግጡ እንስሳት ላይ የሚከሰት ሲሆን በአይን የማይታይ በሽታ አምጪ ህዋሱን በግጦሽ ወቅት ከአፈር ላይ ያገኙታል፡፡ ህዋሱ በአፈር ውስጥ ለረዥም ዓመታት የሚቆይ ስለሆነ የበሽታውን መከላከያ ክትባት ያላገኙ እንስሳት ሊታመሙ ይችላሉ፡፡
- የአባሰንጋ በሽታ ከእንስሳት ወደ ሰው ይተላለፋል፤ አደገኛም ነው፡፡
- በሽታው በአብዛኛው ከመጋቢት አንስቶ እስከ ክረምት መግቢያ ይከሰታል፡፡
- በበሽታው የተያዙ እንስሳት ወይንም ሰዎች በወቅቱ ተገቢውን ህክምና ካላገኙ ለከፍተኛ ህመም ወይም ለሞት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡




# የአባሰንጋ በሽታ

# የአባሰንጋ በሽታ የመተላለፊያ መንገዶች

## የመወያያ ነጥቦች

- ከምስሉ ምን ተረዳችሁ?
- በምስሉ ላይ የምታዩት ሰው በሽታው እንዴት የሚያገኘው ይመስላችኋል? እንስሳቱስ?
- የእንስሳቱ መሞት ከአካባቢ ጋር የሚያገናኘው ነገር ካለ ይግለጹልን



የአባ ሰንጋ በሽታ መተላለፊያ ዑደት

## ቁልፍ መልዕክቶች

- በአባሰንጋ በሽታ አምጪ ተዋስያን ወይም ባክቴሪያ የተበከለን ሥጋ እና የእንስሳት ውጤቶች ጥሬያቸውን ወይም በአግባቡ ሳያበስሉ መመገብ በሽታው ወደሰው እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡
- በባክቴሪያው ከተበከለ/ከተነካካ ቆዳ/ጸጉር፥አጥንት እና ሌሎች ፈሳሾች ጋር ንክኪ መፍጠር በአባሰንጋ በሽታ የሞተ እንስሳ ቆዳና ፀጉር ላይ የሚገኝ ብናኝ ወደ ሳንባችን ሲገባ በሽታው ወደ ሰዎች ይተላለፋል፡፡

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE
Breakthrough ACTION FOR SOCIAL & BEHAVIOR CHANGE

# የአባ ሰንጋ በሽታ መተላለፊያ ዑደት



# የአባሰንጋ በሽታ ምልክቶች በእንስሳት ላይ

## የመወያያ ነጥቦች

- አንድ እንስሳ በአባሰንጋ በሽታ እንደተያዘ እንዴት ልታውቁ ትችላላችሁ?
- አንድ እንስሳ በአባሰንጋ እንደተያዘ ከጠረጠራችሁ ምን ታደርጋላችሁ? ከሞተስ?

## ቁልፍ መልዕክቶች



- በበሽታው የተያዙ እንስሳት በድንገት ለመጋጥ ወይንም ለመጠጣት መቸገር፣ የመተንፈስ መቸገር እንዲሁም አንገታቸው አካባቢ እብጠት ምልክት አሳይተው ወዲያውኑ ይሞታሉ።
- እንስሳቱ ከሞቱ በኋላ በአካላቸው ላይ በሚገኙ የተፈጥሮ ቀዳዳዎች (ዓይን፣ አፍንጫ፣ ፊንጢጣ እና ከመሳሰሉት) በኩል የማይረጋ ደም ይፈሳቸዋል
- በሽታው ወደሰው እንዳይተላለፍ እና ከፍተኛ ጉዳት እንዳያስከትል የታመሙ እንስሳትን ሥጋ ለእርድ ወይንም ለቅርጫ አለማቅረብ፣ ሥጋውንም አለመመገብ ያስፈልጋል።
- በተጨማሪም የታመሙ ወይንም የሞቱ እንስሳትን ተገቢ መከላከያ ሳያደርጉ ወይንም በባዶ እጅ አለመንካት እና በባለሙያ ምክር ታግዞ በአግባቡ መቅበር ወይንም ማቃጠል ያስፈልጋል።
- ያልበሰለ ወይንም ጥሬ ሥጋ አለመብላት እና የሞቱ እንስሳትን ቆዳ ለማንኛውም አገልግሎት አለመጠቀምም በሽታው ወደ ሰው እንዳይተላለፍ ያግዛል።




## የአባሰንጋ በሽታ

# የአባሰንጋ በሽታ ምልክቶች በሰዎች ላይ

## የመወያያ ነጥቦች

- በምስሉ ላይ የምታዩት ምን ይመስላችኋል?
- እነዚህን የሚመስሉ ምልክቶች በራሳችሁ ወይም በካባቢያችሁ በሰዎች ላይ አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- በምን ምክንያት የመጣ ቁስል ይመስላችኋል? ተሞክሮአችሁን አካፍሉ?




## ቁልፍ መልዕክቶች

- የአባሰንጋ በሽታ ወደሰው ከተላለፈ የሚከተሉትን ምልክቶች ሊያሳይ ይችላል።
    - በቆዳ ላይ፦ በበሽታው ከተያዙ ወይንም ከሞቱ እንስሳት ጋር ንክኪ በተደረገበት የሰውነት ቆዳ ላይ ህመም ያለው ከትንንሽ እስከ ትላልቅ ቁስሎች መታየት። ቁስሎቹ ቡናማ ቀለም ያላቸው ሲሆን መሃላቸው ደረቅ ያለ ዙሪያው ውሃ የቋጠረ ሆነው ይታያሉ።
    - የመተንፈሻ እካላት ላይ፦ የእስትንፋስ መታወክ፤ ትኩሳት፥ የደረት ላይ ህመም፥ ድካም እና ደረቅ ሳል ከምልክቶቹ ውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ፤
    - የአንጀት መታወክ ምልክቶች እንደ ማቅለሽለሽ፥ ትውከት፥ ማስቀመጥ፤ ትኩሳት እና የአንጀት መድማትም ሌሎቹ ምልክቶች ናቸው።
- እንዲህ ያሉ ምልክቶች በማንም ሰው ላይ ከታዩ በአፋጣኝ ወደጤና ባለሙያ ሄዶ ህክምና ማግኘት ያስፈልጋል።

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE

Breakthrough ACTION FOR SOCIAL & BEHAVIOR CHANGE



የአባሰንጋ በሽታ

# የአባሰንጋ በሽታ መከላከያ መንገዶች

## የመወያያ ነጥቦች

- ከምስሉ ምን ተረዳችሁ?
- ሰውዬው ምን እያደረገ ነው?
- ምን አይነት አለባበስ አለው? ለምን ይመስላችኋል?




## ቁልፍ መልዕክቶች

- እንስሳትን በአካባቢው ያሉ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች በሚያወጡት መርሀ ግብር መሠረት ማስከተብ፥
- የታመሙ እንስሳትን ሥጋ ለእርድ ወይንም ለቅርጫ አለማቅረብ ሥጋውንም አለመመገብ፥
- የታመሙ ወይንም የሞቱ እንስሳትን ተገቢ መከላከያ ሳያደርጉ ወይንም በባዶ እጅ አለመንካት፥
- ያልበሰለ ወይንም ጥሬ ሥጋ አለመብላት፥
- በአባሰንጋ በሽታ የሞቱ እንስሳትን ቆዳ ለማንኛውም አገልግሎት አለመጠቀም፥
- በአባሰንጋ በሽታ የሞቱ እንስሳትን በድን በባለሙያ ምክር ታግዞ በአግባቡ መቅበር ወይንም ማቃጠል፤



# የአባሰንጋ በሽታ

# የሚያሳብድ የውሻ በሽታ





## የሚያሳብድ የውሻ በሽታ

# የሚያሳብድ የውሻ በሽታ ምንነት

## የመወያያ ነጥቦች

- ምስሉ ላይ ምን ትመለከታላችሁ?
- እንደነዚህ ዓይነት ውሾች በአካባቢያችሁ አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- እነዚህ እንስሳት ምን በሽታ ሊይዛቸው የሚችል ይመስላችኋል? ለምን?
- እንዲህ ዓይነት በሽታዎች በአካባቢያችሁ ሰዎች ላይ ምን ተፅዕኖ የሚኖራቸው ይመስላችኋል?



## ቁልፍ መልዕክቶች

- የሚያሳብድ የውሻ በሽታ በበሽታው ከተያዘ እንስሳ ወደ ሌላ እንስሳ ወይም ወደ ሰው የሚተላለፍ በሽታ ነው:: የሚያሳብድ የውሻ በሽታ መንስዔው በአይን የማይታይ ረቂቅ ህዋስ/ቫይረስ ነው::
- በወቅቱ ተገቢውን ህክምና ካልተወሰደ በሽታው ለሰውም ሆነ ለእንስሳ እጅግ አደገኛና ገዳይ ነው::
- በበሽታው የተያዙ እንስሳት በአካባቢያቸው በሚያገኟቸው እንስሳት ሰዎችም ሆነ ቁሳቁሶች ላይ ይጮሃሉ፣ ሊናከሱ ይሞክራሉ፣ እረፍት እልባ የመሆን አልያም ከተለመደው በተለየ የመፍዘዝ/የመቀዛቀዝ ባሕርይ ያሳያሉ:: በተጨማሪም መዝለፍለፍ፥ መንቀጥቀጥ፥ ለመተንፈስና ለመዋጥ መቸገር፥ የምራቅ መዝረብረብ፥ የመሳሰሉት ምልክቶች ሊታዩባቸው ይችላሉ:: ብርሀን፥ ድምፅና መዳሰስ ያበሳጫቸዋል:: እነዚህ ምልክቶች የታዩባቸው እንስሳት በጥቂት ቀናት ውስጥ ይሞታሉ::



የሚያሳብድ የውሻ በሽታ

# የሚያሳብድ የውሻ በሽታ በሰዎች ላይ

## የመወያያ ነጥቦች

- የሚያሳብድ የውሻ በሽታ የተያዘ ሰው አጋጥሟችሁ ያውቃል? የሚያውቅ ከሆነ እስቲ ያስተዋላችሁትን አካፍሉን
- የሚያሳብድ የውሻ በሽታ ከእንስሳቱ ወደ ሰው እንዴት ይተላለፋል?
- እነዚህን የሚመስሉ ምልክቶች በአካባቢያችሁ በሰዎች ወይንም በእንሳሳት ላይ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ተሞክሮዎን አካፍሉ?



## ቁልፍ መልዕክቶች

- በበሽታው በተያዘ እንስሳ መነከስ ወይም መቧጨር፣ እንዲሁም ከእንስሳቱ ለሃጭ ጋር የሚደረግ ንክኪ በሽታው ወደሰው እንዲተላለፍ ያደርጋል።
- በተለይም በቆዳ ላይ ጭረት ወይንም ቁስለት ካለ የመተላለፉን ሂደት ከፍ ያደርገዋል።
- ትኩሳት፥ ራስ ምታት፥ የድካም ስሜት መሰማት ሕመሙ ሲጀምር የሚታዩ ምልክቶች ናቸው።
- በሽታው ቆየት ሲልም ታማሚው የእንቅልፍ ማጣት፥ የመጨነቅና የመዘበራረቅ ሁኔታዎች ይታዩበታል። በተጨማሪም የተወሰኑ የአካል ክፍሎቹ ወይንም ሙሉ በሙሉ መዛል/ልምሻ ይኖረዋል። ቅዠት፥ የምራቅ መዝረክረክ፥ ሰውንም ሆነ ያገኙትን ነገር ለመተናኮል መሞከር፥ ለመዋጥ መቸገር፥ የመሣሰሉት ምልክቶች ይታያሉ።
- እነዚህ ምልክቶች መታየት በጀመሩ በጥቂት ቀናት ውስጥ ሕመምተኛው ይሞታል።

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE
Breakthrough ACTION FOR SOCIAL & BEHAVIOR CHANGE



የሚያሳብድ የውሻ በሽታ

# የሚያሳብድ የውሻ በሽታን መከላከል

## የመወያያ ነጥቦች

- ከምስሉ ምን ተረዳችሁ?
- የሚያሳብድ የውሻ በሽታን እንዴት መከላከል እንችላለን?




## ቁልፍ መልዕክቶች

- የቤት እንስሳትን (ውሻና ድመት) በየዓመቱ ማስከተብ
- ባለቤት አልባ ውሾች እንዳይኖሩ መከላከል፥
- የቤት እንስሳት ከዱር እንስሳት ጋር ንክኪ እንዳይኖራቸው መጠበቅ
- የማንኛውንም እንስሳ ለሃጭ አለመነካካት
- የቤት እንስሳትን (ውሻና ድመት) ጋር በባዶ እጅ አለመነካካት መነካካት የግድ ከሆነ ከንክኪ በኋላ እጅን በሳሙናና በውሃ በደንብ መታጠብ
- ከማናውቃቸው ውሾች ርቀታችንን በመጠበቅ እንዲሁም ልጆቻችን ውሾችን ከመተንኮስ እንዲቆጠቡ ማድረግ



የሚያሳብድ የውሻ በሽታ

# የብሩሴሎስስ ወይንም የውርጃ በሽታ





## የውርጃ በሽታ (ብሩሴሎስስ)

# ብሩሴሎሲስ ወይም የውርጃ በሽታ ምንነት

## የመወያያ ነጥቦች

- ከምስሉ ምን ተረዳችሁ?
- በአካባቢያችሁ በአብዛኛው የትኞቹ እንስሳቶች ያስወርዳቸዋል? በምን ምክንያት የሚያስወርዱ ይመስላችኋል?
- ከወተት እና የወተት ውጤቶትች ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ በሽታዎች ምን ምን ታውቃላችሁ?

## ቁልፍ መልዕክቶች

- ብሩሴሎስስ ወይንም የውርጃ በሽታ በአይን የማይታዩ ረቂቅ ህዋሳት/ ባክቴሪያ አማካኝነት በዋናነት የእንስሳትን የመራቢያ አካላቸውን የሚያጠቃ ተላላፊ በሽታ ነው::
- የብሩሴሎሲስ በሽታ ከእንስሳት ወደ እንስሳት እና ከእንስሳት ወደ ሰዎች ይተላለፋል::
- በሽታው ካለባቸው እንስሳት የሚወጡ ፈሳሾች በተለይ ደም፤ ወተትና የወተት ውጤቶች እንዲሁም የእንግዴ ልጅ ዋነኛ የበሽታ አምጪ ህዋሱ በብዛት የሚገኝባቸው ክፍሎች ናቸው::





የውርጃ በሽታ (ብሩሴሎሰስ)

# የውርጃ በሽታ ምልክቶች

## የመወያያ ነጥቦች

- በምስሉ ላይ ምን ትመለከታላችሁ?
- እርግዝናው ከስድስት ወር በላይ የሆነው የእንስሳ ጽንስ በምን ምክንያት የሚወርድ ይመስላችኋል?



## ቁልፍ መልዕክቶች

### በእንስሳት ላይ

- ሴት እንስሳት ላይ ተደጋጋሚ ማስወረድ ይታይባቸዋል
- ወንዶቹ ላይ ደግሞ የመራቢያ አካላት እና በጉልበታቸው ላይ እብጠት ሊታይባቸው ይችላል።

### በሰዎች ላይ

- በሽታው ሲከሰት እንደአንዳንድ ትኩሳት እና ህመም አምጪ በሽታዎች ለረዥም ቀናት የሚቆይ ትኩሳት፤ የመገጣጠሚያ አካላት ቁርጥማት፤ የድካም ስሜት፤ የምግብ ፍላጎት መቀነስ ያሉ ምልክቶችን ያሳያል።



የውርጃ በሽታ (ብሩሴሎሲስ)

# የውርጃ በሽታ የመተላለፊያ መንገዶች

## የመወያያ ነጥቦች

- በአካባቢያችሁ ሰዎች ወተት ከመጠጣታቸው በፊት ምን ያደርጋሉ? ለምን?
- አንድ ከብት ከመሞቱ በፊትስ ምን ይደረጋል?
- እነዚህን ማድረጉ ምን ችግር አለው?
- የውርጃ በሽታ በምን በምን መንገዶች የሚተላለፍ ይመስላችኋል?



## ቁልፍ መልዕክቶች

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዋና ዋና የውርጃ በሽታ ማስተላለፊያ መንገዶች ናቸው

- ከውርጃ ጋር የተያያዙ ፈሳሾች፤ ደም እና ሌሎች የውርጃው ቅሪቶች እንዲሁም የተበከለ አካባቢ (አፈርና ውሃ) ጋር የሚደርግ ጥንቃቄ የጎደለው ንክኪ
- ወተት እና የወተት ተዋፅኦዎችን በአግባቡ ሳያበስሉ መመገብ
- ከሰው ወደ ሰው፤ በደም ንክኪ



## የውርጃ በሽታ (ብሩሴሎሲስ)

# የውርጃ በሽታ መከላከያ መንገዶች

## የመወያያ ነጥቦች

- የውርጃ በሽታን ምን በማድረግ መከላከል ይቻላል?
- ከምስሉ ምን ተረዳችሁ?

## ቁልፍ መልዕክቶች

- ወተት እና የወተት ተዋፅኦዎችን በአግባቡ አፍልቶ ወይንም አብስሎ መመገብ፡፡
- እንስሳትን በምናዋልድበት ወቅት እጃችንን እና አፋችንን መሸፈን፤ ሌላው የሰውነት ክፍላችንም እንዳይነካካ ጥንቃቄ ማድረግ
- ከእንስሳት ጋር የምናደርገው ንክኪ ተገቢ የሆነ መከላከያ ባለው መልኩ እንዲሆን ማድረግ፥
- ካስወረዳት እንስሳ የሚወጣውን ማናቸውንም ነገሮች እንደ ደም እና ሌሎች ፈሳሽ ነገሮች አካባቢውን እንዳይበክሉ በደንብ ማፅዳት እና በጠንካራ ላስቲክ ጠቅልሎ መቅበር ወይንም ማቃጠል፡፡
- ከውርጃው ወይንም ከፈሳሹ ጋር ንክኪ ያላቸውን ልብሶች፣ ቢላዋ ወይም ሌላ ማናቸውም ነገሮች በተገቢው ሁኔታ ተዘፍዝፎ ማጠብ፡፡



